ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
የሰሜን አሜሪካ ተጠሪ ጽ/ቤት
Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)
North America Representative Office

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## በሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ዉስጥ ቅንጅት ኢንተርናሽናል አመራር በፈጠረዉ ችግር የተወሰደ ዉሳኔ

ወድ ኢትዮጲያዊያን ወገኖቼ ፥

የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ከተቋቋመ እነሆ አንድ ዓመት በላይ ሆኖታል። ለተወሰኑ ወራቶች እንደዚሁም ከዚያም በፊት ቅንጅትን በፈጠሩት አባል ድርጅቶች አማካኝነት ለግንቦት 1997 ምርጫ ለመሳተፍ ጥረት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በገንዘብ በቁሳቁስና እንደዚሁም የዓለም አቀፍ ሕብረተሰቡን ስላገራችን የፖለቲካ ችግር በማሳሰብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ፲ በማድረግም ላይ ይገኛል።

በአዉሮፓም ሆነ በሌሎች ክፍለ ዓለማት ተመሳሳይ ድርጊቶች በመፈጸማቸዉ ጥሩ ዉጤቶች ተመዝግቧል። ዛሬ በአሜሪካ ብቻ እስከ 25 የሚደርሱ የተጠናከሩና ዕዉቅና ያገኙ የድጋፍ ድርጅቶች ሲኖሩ ፲ በሌላዉ ዓለም አቀፍ ከተሞች በአመዛኙ በራሳቸዉ አነሳሺነት የተቋቋሙ የቅንጀት ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎች ይገኛሉ።

እነዚህ ዉጪ አገር ያሉ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በተጠናከረ ኃይል መሪዎቻችንን ለማስፈታት ለዲሞክራሲ መብቶች የሚደረገዉን ትግል ለመርዳት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። የሰሜን አሜሪካም በበኩሉ የአሠራር ስልቱን መዋቅሩንና የመተዳደሪያ ደንቡን በማዘጋጀት ላይ እንዳለ ችግሮች መከሰት ጀመሩ።

ይኸዉም በወቅቱ የቅንጅት ደጋፊ ነኝ በሚል ስም በመሀከላችን እንዲቀላቀል የተቀበልነዉ አቶ ብርሃነ መዋ አባላችን ከሆነ ከጥቂት ወራቶች በኋላ ኮሚቴዉን ሳያሳዉቅ በግል የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች ከፍተኛ ጥርጣሬዎችን ሲያሳድርብን ቆይቷል። ዘግየት ብሎም ከአቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ጋር በማበር አመጣጡ እስካሁን ግራ ያጋባንን ቅንጅት ኢንተርናሽናልን ፈጥረዉና አስገዳጅ ሁንታዎችን አመቻችተዉ ዛሬ በዚሁ ድርጅት ጥላ ሥር ጎጂ ተግባራትን እያራመዱና የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ አካላትን እያበጣበጡና እየበታተኑ ይገኛሉ።

8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD 20910
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090, Email: KinijitUSA@Kinijit.org

ይኸውም ፤

1ኛ ፡ በስንት ልፋትና ድካም የተቋቋሙትንና ለትግሉ ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱ የድጋፍ ኮሚቴዎቻችንን በረቀቀና በስዉር ዘዴ ለማፈራረስ ፣ አባላቱንና መሪዎቹን በማጋጨትና በመበታተን ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ነዉ። ከአመራሩ ሳይመከሩና የመተዳደሪያ ደንባችን ጸድቆ ስለ ምልመላና አደረጃጀት ፣ ስለ ድጋፍ ድርጅቶች ሚናና በላይነት (እዝ ሰንሰለት) ዉሳኔ ሳይሰጥና ስምምነት ሳይደረስ ለአፍራሽ አላማቸዉ ስኬታ አባላቱን በፓርቲ መልክ እናደራጃለን በማለት ያልጠረጠሩና ያላወቁ ወገኖቻችንን በተለይም ወጣቱን ክፍል አሁንም በምስጢር በመመልመል ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም እነዚሁኑ ግለሰቦች በመጠቀም ጠንካራ የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶቻችንን ለማፈራረስ መሪዎቹ በሃሰት ክስ እንዲወነጃጀሉ በማድረግ ላይ ናቸዉ።

ይህ አካሄድ አደገኛና አምባገነናዊ ከመሆኑም በላይ የቅንጅትን መሪዎች ሕይወታቸዉን ለሰጡለት ዲሞክራሲያዊ ፍልስፍናና ሂደት ፍፁም ተፃራሪ ነዉ። ይህ እንቅስቃሴያቸዉ በፈጠረዉ ዉዥንብር ምክንያት ለታሠሩት መሪዎቻችንና በጭንቀት ላይ ላለዉ የኢትዮጲያ ሕዝብ ማድረግ ያለብንን ትግል ወደፊት ለማራመድ እንቅፋት ሆኗል። በዚሁ የአዲስ ፓርቲ ምልመላቸዉ ሂደት በርካታ የወያኔ ወኪሎች እየተሰገሰጉ ለመሆኑም መረጃዎች እየቀረቡ ነዉ።

2ኛ ፡ በዉጪዉ ዓለም የቅንጅት ስብስብ ከሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት ጋር ተባብረዉ እንዳይሠሩ ተንኮል የተሞላበትን የተናጠል እርምጃና ዉሳኔ በማድረግ ቅንጅቱን አኮላሽተዉ ለማስቀረት ጥረት ሲያደርጉ ታይተዋል።

3ኛ ፡ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተያዘዉን ያባላትንና የደጋፊዎችን መረጃ በጥንቃቄ ባዘጋጁበት ቅጽ አመራሩን ሳያማክሩ ለመሰብሰብ ለምን እንደፈለጉ ሲያጠራጥረን ከርሟል።

4ኛ ፡ የታሠሩ መሪዎቻችንን በከፍተኛ አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ እያሉ ከነሱ ያልሆኑ መልክቶችን ከነሱ እንደመጡ በማስመሰል በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ጭምር በማሰራጨት ጉዳት አድርሰዋል።

5ኛ ፡ በእሥረኞች ስም በመጠቀም በግል ያላቸዉን የሥልጣን ጥማትና አምባገነንነት ባሕርይ በማያሻማ ሁኔታ ለአባላትና ለደጋፊዎቻችን አሳይተዋል።

6ኛ ፡ ከቅንጅት ፍልስፍናና እምነት ዉጭ ሁኔታዎችን ባልጠረጠሩና ባልተገነዘቡ ወገኖች መሃከል በስዉር የቴሌኮንፍርንስ ስብሰባ በማድረግ የዉጪዉን ድጋፍ እንቅስቃሴ ለመስበር ጥረት ሲያደርጉ በተጨባጭ ማስረጃ ተደርሶባቸዋል። ቴሌኮንፍርንሶቹ ብዙ ሲሆኑ ፣ በቅርብ የሆኑት October 9 & 12, 2006 ናቸዉ።

7ኛ ፡ ከወያኔ አባላትና እንዲሁም ቅንጅትን ከድተዉ የወያኔ መሣሪያ ከሆኑ ግለሰቦች ጋር የስዉር ግኑኝነት ማድረጋቸዉ እንቅስቃሴአችንን አደጋ ላይ እንደሚጥለዉ ተገንዝበናል።

**8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD 20910**
**Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090, Email: KinijitUSA@Kinijit.org**

ዉድ ወገኖቼ፦
የኢትዮጲያ ሕዝብና የታሠሩት ወገኖቻችን የጣሉብንን ከፍተኛ ኀላፊነትና አደራ ለመወጣት በቅድሚያ በምክርና በዝክር ችግሮችን ለመፍታት ብዙ ግዜ አባክነን ፣ አሁን ግን አስቸኳይ እርምጃን መዉሰዱ አማራጭ የሌለዉ መሆኑን ተረድቻለሁ። ስለሆነም ማንኛዉም የቅንጅት ኢንተርናሽናል እንቅስቃሴ ሁኔታዉ እስከሚጣራ ድረስ ላልተወሰነ ግዜ የታገደ መሆኑን አስታዉቃለሁ።  በተጨማሪም ለሥልጣን ጥማቸዉና የአምባገነንነት ፍላጎታቸዉን ማርኪያ ብለዉ በጭንቀት ላይ ያሉ መሪዎቻችንን በመጎትጎትና በማደናገር እንዲቋቋም የተደረገዉ ቅንጅት ኢንተርናሽናል አባል የሆኑት አቶ ብርሃነ መዋና አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ በቅንጅት ሰም በሰሜን አሜሪካ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላልተወሰነ ግዜ የታገደ መሆኑን አስታዉቃለሁ።

የበለጠ ዝርዝር መረጃና ማብራርያ በማከታተል ይሰጣል። የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ እንቅስቃሴም በተጠናከረና በተጣራ መልኩ እንደሚቀጥል ለአባሎቻችንና ለደጋፊዎቻችን ለማሳወቅ እወዳለሁ።

ስለሆነም ፣ የቅንጅት ቻፕተሮችና ደጋፊዎች በሙሉ ፤

1ኛ ፡ ማናቸዉም የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ዕርዳታ ለነዚህ ግለሰቦች እንዳይሰጡ ፣

2ኛ ፡ የቅንጅት ዉክልና በማናቸዉም መስኩ የሌላቸዉ ለመሆኑ እንዲታወቅ በትህትና እያሳሰብኩ ፣

3ኛ ፡ ይህንንም ዉሳኔ ለመሪዎቻችን ያሳወቅሁ መሆኑን እገልፃለሁ ።

**ድል ለኢትዮጲያ ሕዝብ !**

ሻለቃ ዮሴፍ ያዘዉ

የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ሊቀመንበር
የቅንጅት ዓለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ሊቀመንበር

October 15, 2006

**8605 Cameron Street, Suite M – 0, Silver Spring, MD 20910**
**Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090, Email: KinijitUSA@Kinijit.org**